ጥቅምት 8 ቀን 2002 ዓ.ም

# እኛ ስንዋደድ!

## ከ40.000 በላይ በታደሙ የሙዚቃ ዕድምተኞች፣ የአዲስ አበባ ስታዲዮም ተጨናነቀ!

## ብራቮ ቴዲ አፍሮ - ቪቫ ኢትዮጵያዊነት!

ከአያልነሽ

*"በዚህ ምድር ያደረግነው በዚህ ምድር ይቀራል። ከምድር በላይ ያደረግነው ደግሞ ሁሉም ይኖራል"*

*ቴዲ አፍሮ ከተናገረው የተቀነጨበ*

የብዙኃኑን ኢትዮጵያዊ ለቅሶ የሚያነባው ቴዲ፣ ዛሬም ከ18 ወር እስር ቤት ቆይታው በኋላ በመድረክ ላይ ወጥቶ በችግር የሚጥመነመኑ አዳጊዎችን "ለግማሽ ጎኔ፣ ካለኝ ቀንሽ ለወገኔ" በማለት ለቅሷቸውንና ረኃባቸውን አብሮ ተካፈለ! አነባ። የቴዲ ልብ እጅግ ሥስ ነች፣ እጅግም ደግሞ ቀና የፍቅር ልብ! ታዲያ ይሄንን የመሰለ የባህሪ ገንዘብ ይታደሉታል እንጂ ይታገሉታልን?!

በሙዚቃ ክህሎቱና መላ አካላትን በሚነዝረው ቅላጼው የምናውቀውና የሚታወቀው ቴዎድሮስ ካሣሁን (ቴዲ አፍሮ)፤ ገቢው በችግርና "በልመና" ለተሠማሩ አዳጊ እምቦቃቅላዎች ይውል ዘንድ ባዘጋጀው የሙዚቃ ምሽት (ኮንሰረት)ላይ፣ ከ40.000 በላይ የሚገመት የሙዚቃው ታዳሚ የአዲስ አበባን ስታድዮም አጨናንቋት ሠንበተ። ቴዲ ለሚወዳቸውና ለሚያከበራቸው የሙዚቃው ታዳሚዎችም ሆነ ለኢትዮጵያ ሕዝብ በሙዚቃው ቅላጼ ሊያስደስታቸው ሲነሳና ሲዘጋጅ፣ አብሮት የማይለየውና አብሮት የተፈጠረ የሚመስለው ትህትናውም ዛሬም አልነጠፈም። ይልቁንም ፈክቶና ደምቆ የታዳሚውን ልብ አስደምሟል፣ ሰብሯልም። በእርግጠኝነት ማለት የሚቻለው ስለ ቴዲ፣ ትህትናው ሞልቶ የፈሠሠ ነው። አቦ! ከክፉ ዓይን ይሰውርህ ጃል!




ቴዲ ሌላም የተላበሰው ፀጋ አለ። በዕድሜው ወጣት፣ በስብዕናው ግን ታላቅ ሆኖ የሚታየው ቴዲ ለዚህ ሰብዕናውና ትህትናው ምስሶውና ምስጢሩ፣ ለሰው ልጅ የመጨነቁ ባህሪውና ይህም ባህሪው የዘወትር ልብሱና ካባው የማድረግ ችሎታው ነው። በሌሎች ላይ የሚደርሰው ፈተና ይኸው በእርሱም ላይ ደርሶበት በቅርቡ ቴዲን ሊጋፈጠው የመጣና የዳሰሰውም

መከራ፣ ገና በለጋነት ዕድሜው ላይ ሆኖ ነው። ላይችል አይሰጥ ይባል የለ!

ቴዲ 1 ዓመት ከ 4 ወር ገደማ እሥር ቤት እንዲቆይ የተደረገበት ይኸው መከራ፤ *"ያለ መንጃ ፈቃድ መኪና በማሽከርከርና ሰው ገጭቶ በመሸሽ"* የሚል የሐሰት ክስ በወያኔ ተቀነባብሮ በቀረበበት ወቅት፤ ይህንን የሐሰት ክስ እንዲህ በማለት ማጣጣሉ አይዘነጋም።

> *"እኔ ይህ ተፈፀም የተባለው ድርጊት በተፈጸመበት ቦታ አልነበርኩም፤ በተጨማሪም ክቡር የሆነውን ሰው ሕይወት ገደይ ወይም ገጨቼ የምሸሽ ሰውም አይደለሁም። ይልቁንም ክቡር በሆነው የሰው ሕይወት ላይ ይህንን መሰል ከባድ ወንጀልና ድርጊት ፈጽመኃል ተብሎ መከሰሴ፣ ክበሬን የሚነካና ሰብዕናዬንም የሚያጎድፍ ነው....."*

*ብሎ ነበር*

ታዲያ! ያኔ ያኔ ቴዲ በ18 ወራት የእስር ቤት ቆይታው (ወያኔ ይህንን ሰዎችን የሚያጉርበትን እስር ቤቱን ማረሚያ ቤት ይለዋል) ወቅት፣ በቀጠሮ ወደ የይስሙላው ፍርድ ቤት ቅፅር ግቢ በሚመላለሰበት ጊዜ፣ ዛሬ ይህንን የቴዲን የሙዚቃ ድግሥ ሊቋደሱ የአዲስ አበባን ስታዲዮም ያጥለቀለቁት ወጣቶችም አብረው በችሎቱ አደባባይ ተኮልኩለው የቴዲን ጭንቅ ይካፈሉ ነበር። "ቴዲ ነፃ ሰው ነው፤ ቴዲ ለድኃ የቆመ የደኃ ጠበቃ እንጅ ደኃን የሚገደል አይደለም " እያሉም የቴዲን አለአግባብ መታሠር በከፍተኛ ቁጣና በኃለ የወገንተኝነት ስሜት ለቴዲ ያላቸውን አክብሮት በመግለጽ ድርጊቱንም አምርረው ያወግዙ ነበር...። በዚያን ወቅትም ቢሆን እነኝህ ወጣቶች በወያኔ የፖሊስ ዱላ ይደበደቡና ይነረቱ እንደነበር በየጊዜው በሚድያ ሲነገርና ሲዘገብ የቆየ የማይደበቅ እውነታ ነው። ለሚወድ ሰው መወደድን ያገኛል። ለሚያዝን ሰው አዛኝ ልብ ይቸረዋል/ያገኛል። ለቴዲም ከአድናቂዎቹና ከብዙኃኑ የሚልገሠው ስጦታ ገንዘብ አይደለም- ከብዙኃኑ ልብ ውስጥ የመቀመጥ ፀጋን እንጅ። ።"የሰው መውደድ ይሰጠኝ" ነው የሚለው የሀገሬ ሰው። ከተወደዱ አይቀር እንዲህ ነው - እንደ ቴዲ፣ በበጎ ሥራ፣ በቀናነት፣ ከልብ በሚመንጭ ትሁትነትና ቀና ልብን ለጋሥነት። "ስልጡንና ዘመናዊ ነን" ባዮች ከቴዲ ምን ይማራሉ..? ምንስ እንማራለን! ብራቮ በድጋሚ.....ቴዲ አፍሮ!

የቴዲ አድናቂ ብዙኃን ነው፣ የቴዲ አድናቂ ከወጣት እስከ አዕሩግ ነው። የቴዲ አድናቂ የዘር አጥርን የበጣጠሰና የደረመሰ ነው። የቴዲ አድናቂ ድኃና ኃብታሙንም እኩል አቁሟል። የቴዲ አዳናቂ የተለያዩ ኃይማኖት ያላቸውን ኢትዮጵያዊያንንም የሙዚቃው ምርኮኛ አድርጓል የቴዲ አድናቂ ባሕር ማዶንም ተሻግሮ አስተሳስሯል፤ አያይዟል። ምን አለፋችሁ ቴዲ የእናቱ ብቻ አይደለም፣ የሁሉም ነው። የቴዲ አድናቂ የኢትዮጵያ ህዝብ በሙሉ ነው - ወይ ትንግርት! ታዲያ እንዲህ ከሆነ ዘንዳ የኢትዮጵያን ሕዝብ በሙሉ መጨረስ ይቻላልን...? ዘበትና የግብዞች የማይጨበጥ ሕልም። ለዚህም ነው ቴዲ ንብረትነቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው የምለው።

በዚህ የአዲስ አበባ ስታድዮም ታጭቆ ለነበረውና መንቀሳቀሻ፣ መሠናዘሪያና የጠጠር መጣያ ቦታ እንኳን ላልነበረው የሙዚቃው ታዳሚ ከ 25 በላይ የተለያዩ ሙዚቃዎችን ተጫውቷል። ቴዲ ወደ መድረኩ ሲወጣና ብቅ ሲልም ከሙዚቃ ታዳሚዎቹ ዘንድ የወጣው አስገምጋሚው ጭኸትና ፉጨት ነጎድጓዳዊ ብራቅ ያክል አስተግብቷል። በስታዲዮሙ ውስጥ ከነበረው ከ40 ሺህ በላይ ከሚገመተው የሙዚቃ ታዳሚ ይልቅ ደግሞ ከስታዲዮሙ ውጭ የነበረው ህዝብም፣ አካባቢውን በጩኸት አናውጦታል። ..... ቴዲ ....ቴዲ..... ቴዲ .....እያለም በሲቃ ስሜቱን ሲገልጽ ነበር። የቴዲን በረከት ከ40 ሺህ በላይ በስታዲዮሙ ውስጥ ተገኝቶ ከተከታተለው ይልቅ ከስታዲዮሙ ውጭ የነበረው ሕዘብ፣ አቅም ያለው በየመብራት መሰሶዎች ላይ እየተንተላጠለ፣ አቅም የሌለው ደግሞ እንዲሁ ጆሮን ሰርስሮ በሚነዝረው የቴዲ ስርቅርቅ ድምፅ ተደምሞ አምሽቷል። ለቴዲ ያላቸውን

ክብርም ዛሬም ቢሆን ያሳዩበት አጋጣሚ ነው ማለት ይቻላል። እርግጥ ነው ቴዲም የእነርሱ፣ እነርሱም የቴዲ ናችውና! እናመሠግንኃለን ቴዲ!

ቴዲ ወዲህ ወደ አውሮፓና አሜሪካም ይሻገራል ተብሎ በጉጉት እየተጠበቀ ነው፤ ይህ የከበረና የደመቀው ዕንቁ ንብረታችንና ሀብታችን ሲመጣ ደግሞ፣ እቅፍ ድግፍ አድርገን እንቅፋት እንዳይመታው የማደረጉ ኃላፊነት የኛው የወገኖቹ የኢትዮጵያዊያን ተግባርና አደራ ይሆናል ማለት ነው። ዕንቁ የሆነውን አሴቱን የማይንከባከብና የማይጠብቅ ዜጋ ምን ይባላል...... ? ለጥያቄዬ የሚሆን መልስ ያላችሁ የምታውቁትን ሙሉትና .....እኔም ጨዋታዬን ልቋጭ።

## ጃ!ያስተሠርያል! ብራቮ ቴዲ አፍሮ! ቪቫ- ኢትዮጵያዊነት!

የሕዝብ ድምፅ ይክበር፣ የታሠሩ የፖለቲካ እስረኞች በሙሉ ይፈቱ!
ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!
ቸር ይግጠመን

ኦክቶበር 18/ 2009